9. Baantanni baatooshshi aaninni xeinse baantanni takise woy layinki deerri gadachonni baantanni takise aana hendanni keeshshino baatooshshi qallo baatama noosihu kuni gadachi noosi manchinni calla ikkinohura wolu aye manchiwiinnni xa'ma didandiinanni.

10. Keeshshino baatooshshi aana tunganni qallo xaphoomu bikki takisete baataanchi takisete asale roorara didandaanno.

11. Konni quwi hexxora ''takise'' keeshshino baatooshshi aana hendanni qallo dilendanno.

Foolliishsho Sase

BaantonnikkitaTakise Baatisiisa

38. Takisete Shallaguwa Gumulisiisannire

1. Konni quwi cinaancho quwa 2 noo garinni hee'reenna takisete baataasinchi konni lallawi quwa 55 xawinsoonni yanna giddo koffeenya shiqisha hoogiro biilto takisete baataanchira uytanno takisete shallago koffeenya shiqishi'rate yanna gooffu barrinni kayse goofimarchunnihanna gumulamme nooha ikkanno.

2. Takisete baataasinchi takisete shallago aana koffeenya shiqishiro, takisete herrego woroonni noo ikkitubbanni keeshshino gumulammete yanna goofimarcho ikkitanno:-

ስሌት ማስታወቂያን ጨምሮ በማንኛውም የጽሑፍ ማስታወቂያ ያሳወቀው እንደሆነ፤ እና

ለ) ታክስ ከፋዩ ማስታወቂያው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ መክፈል የሚጠበቅበትን የዘገየ ክፍያ ወለድ ጨምሮ በማስታወቂያው የተመለከተውን የታክስ ዕዳ በሙሉ በማስታወቂያው በተገለጸው የመክፈያ ቀን የከፈለ ከሆነ፤

9. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት በሚከፈል ታክስ ላይ የሚታሰብ የዘገየ ክፍያ ወለድ መከፈል ያለበት ይኸው ኃላፊነት ባለበት ሰው ብቻ በመሆኑ ከሌላ ማንኛውም ሰው ሊጠየቅ አይችልም።

10. በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን ከታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ሊበልጥ አይችልም።

11.ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ታክስ" በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድን አይጨምርም።

ምዕራፍ ሦስት

ያልተከፈለን ታክስ ስለማስከፈል

38. የታክስ ስሌቶችን ስለማስፈጸም

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቅሬታ ካላቀረበ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የሚሰጠው የታክስ ስሌት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ የመጨረሻ እና ተፈጻሚነት ያለው ይሆናል።

2. ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታ ካቀረበ፣ የታክስ ስሌቱ ከሚከተሉት

A) Takisete baataasinchi takisete kado/ yigibanye/ komishiinete takisete shallago aana kado shiqisha hoogiro, konni lallawi quwa 87 la'noonnihu kado/yigibbanye/ shiqishate yanna gooffuro,
B) Takisete baataasinchi takisete kado/yigibaanye/ komishiine takisete herrego aana kado shiqishiriro, konni lallawi quwa 57 xawinsoonnihu qoqqowunna aliidi yoo minira kado/ yigibanye/ shiqqanno yanna gooffuro,
C) Takisete baataasinchi aliidi yoo minira takisete shallago aana kado shiqishiriro; konni lallawi quwa 58 xawinsoonnihu qoqqowu xaphoomu yoo mine kado shiqishanno yanna gooffuro woy
D) Takisete baataasinchi qoqqowu xaphooma yoo mine takisete herrego aana kado shiqishi'riro, yoote mini goofimarchu gumulo uyro.

3. Konni quwi cinaanchu quwa 2 danaggangoonnihu yekkeerote aana noo takise konni lallawi quwa 56 (2) nna 57(5) garinni baatatenni dihoollanni.
4. Goofimarchunniha ikkitino takisete shallago hasi'nannisi takise konni quwi cinaancho quwa 1 nna 2 garinni baatantinokki takise baataasinchi gadachosi fulinokkiha takisete asale ikkanno.

39. Jirote Aana Shiqqannota Balaxate Qoosso Xa'mo

1. Konni quwi cinaanchu quwa 2 nna la''annonsa bissa maareekkisiissino ay balaxino woowishsha uynoonni qoosso agarantino

የዘገየው ሁኔታ በተፈጸመበት ጊዜ የመጨረሻ ይሆናል፡-

ሀ) ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካለቀረበ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 87 የተመለከተው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሲጠናቀቅ፣
ለ) ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 የተመለከተው ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ፣
ሐ) ታክስ ከፋዩ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 የተመለከተው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ፣ ወይም
መ) ታክስ ከፋዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ በክርክር ላይ ያለን ታክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 (2) እና 57 (5) መሠረት ከመክፈል አይከለክልም፡፡
4. የመጨረሻ በሆነ የታክስ ስሌት የሚፈለግበትን ታክስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ያልከፈል ታክስ ከፋይ ግዴታውን ያልተወጣ የታክስ ባለዕዳ ይሆናል፡፡

39. በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና በሚመለከተው አካል የተመዘገበ ማንኛውም የቀደመ ዋስትና የተሰጠበት መብት

gedeenni heedheenna takisete higge /seeri garinni takisete baataasinchi baata hasiissanno baatate yanna iillitino takise wo'ma baaate guda geeshsha biilto takisete baataasinchi jiro aana balaxooshshu qoosso heedhannose.

2. Konni quwi cinaancho quwa 1 worroonih balaxote woowishshira uynoonni qoosso baankuwa woowishsha adhitino woxu xa'mubbana qaxaramaasinete damoozu balaxote qoosso ledanno. Ikkeennano konni lallawi quwa 33/1/A/ la'noonni takisubba ledo xaaddinohunni gumulamannoha di''ikkanno.
3. Ayno takisete baataasinchi takise baatate gadacho fulinokki ikkiro biilto baatinokki takisenna takise baatisiisate adhitanno qaafo fushshiishshanno fulo baatisiisa dandiitanno gede takisete baataasinchi jiro aana biiltote woowishshu qoosso maareekkisiissanno gede jajja maareekkitanno bissara qummisanno gede xawisanno egensiishsha takisete baataasinchira uynanni.
4. Konni quwi cinaanchu quwa (3) xawinsoonni egensiishshi iillinosi takisete baataasinchi egensiishshu iillihunni 30 barri giddo takise baatinokkiha ikkiro, biilto takisete baataasinchira uynoonni egensiishsha leellinshonniti takisete baataasinchi jiro baataminokki takisenna takse baatisiisate aasinanni fulora woowishshunni amadanno gede jajja maareekkitanno bissara borrote hajajo aanno.
5. Konni quwi cinaanchu quwa (4) garinni biilto takise hasidhanno manchi jiro woowishshunni amadde keeshshiishshanno hajajo uytanno

እንደተጠበቁ ሆነው፣ በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባው የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የቀደመ ዋስትና የተሰጠበት መብት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው የገንዘብ ጥያቄዎችና የተቀጣሪዎችን የደመወዝ የቅድሚያ መብት ይጨምራል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 (1) (ሀ) ከተመለከቱት ታክሶች ጋር በተገናኘ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
3. ማንኛውም ታክስ ከፋይ ታክስ የመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለውን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚወሰደው እርምጃ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የባለሥልጣኑን የዋስትና መብት እንዲመዘግብ ንብረቱን ለመዘገበው አካል እንደሚያመለክት የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፀው ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተው የታክስ ከፋዩ ሀብት ላልተከፈለው ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል ለሚደረግ ወጪ በዋስትና እንዲያዝ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የጽሁፍ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ባለሥልጣኑ ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ

yannara maareekkaanchu biilchi jiro woowishshunni amandanni gede iillitinosi borrote hajajo ay dani baatooshshe xa’mikkinni ay dani jirote aana noo jajja amadate woy woowishshu sanadera borreessanno, umo assine uynoonni amadate qoosso noowa heedheenna, amadate woy woowishshu maareekko hasi’nanni takise baatisiisate ay daninino higgete/seeruy uynoni amadate woy woowe ikke kiiramanno.

6. Biilto konni quwi cinaanchu quwi (5) garinni woowishshuni buuxinsoonni takise wo’ma adhitano wote biilto maareekkaanchu biilloonyi konni quwi cinaanchu quwa (4) hunda uynoonnisi hajajo garinni assino maareekko sarrazanno woy rige hunanno gede egensiishsha aannoha ikkanna maareekkaanchu biilloonyunno baatooshshiweelo woowishshu maareekko sarrazanno woy rige hnanno.
7. Konni quwi cinaanchu quwa (2) garinni baankootu woowishsha adhitino jirora balaxote qoosso heedhannonsahu liqoo aate albaanni takisete baataanchi asalu noosikkiha ikkasi biiltotenni buuxaminoha I kkiro callaati.

40. **Tarakkabbawori Gadacho**

1. Ayee tarakkawanchino, mittu takisete baataannchi jiro Itiyophiyu giddo tarakkawannoha ikke mootoo’miro woy jirosi amadosi woroonni e’uro lamunkuy balaxxawo yannayi hanafe noo 14 (tonaa shoole barruwa) giddo biilloonyeho borrotenni egensiisa noosi.
2. Biilloonyu jirosi terakkawaanchu woroonni noosi takisete baataanchi baantoonnikki takisete asalenna albillitte baantanni takisete

በሚሰጥበት ጊዜ መዝጋቢው ባለሥልጣን ሀብቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን የጽሑፍ ትዕዛዝ ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይጠይቅ እንደማንኛውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የንብረት መያዣ ወይም የዋስትና ሰነድ ይመዘግባል፤ ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመያዣው ወይም የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም ዋስትና ሆኖ ይቆጠራል።

6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት በዋስትና የተረጋገጠውን ታክስ በሙሉ ሲቀበል ባለሥልጣኑ መዝጋቢው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ሥር በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያካሄደውን ምዝገባ እንዲሰረዘው ማስታወቂያ የሚሰጠው ሲሆን መዝጋቢው ባለሥልጣንም ያለ ምንም ክፍያ የዋስትናውን ምዝገባ ይሰርዛል።
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው ሀብቶች የቀደምትነት መብት የሚኖራቸው ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው።

40. **የተረካቢዎች ግዴታዎች**

1. ማንኛውም ተረካቢ የአንድን ታክስ ከፋይ ሀብት በኢትዮጵያ ውስጥ ተረካቢ ሆኖ ከተሾመ ወይም ሀብቱ በይዞታው ሥር ከገባ ከሁለቱ ከሚቀድመው ጊዜ ጀምሮ ባሉት 14 (አሥራ አራት ቀናት) ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
2. ባለሥልጣኑ ሀብቱ በተረካቢው ቁጥጥር ሥር ባለው ታክስ ከፋይ ያልተከፈለውን የታክስ ዕዳ እና ወደፊት የሚከፈለውን የታክስ መጠን በመወሰን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)

jilba muratenni konni quwi cinaanchu quwi (1) xawinsoonni borrote egensiishshi iillihunni 30 barri giddo tarakkawanchoho egensiisa noosi.

3. Konni quwi cinaanchu quwi (4) noo geenni heereenna, tarakawaanchu;
   a) Biiloonyunniwiinni balaxe fajjo afira hoogiro angasi afamanno takisete baataanchi jiro konni quwi cinaanchu quwi (2) leellinshonni egensiishshi iillisikki woy egensiishsha uyinisikki konni quwi cinaanchu quwi (2)worronniha 30 (sajjoo) barri yanna sa’ate albaa hira woy ayee garinni sayisa didandaanno.
   b) Jirote hiro woxi aaninni biilloonyu konni quwi cinaanchu quwi (2) garinni xawisinoha takisete bikka woy biilloonyu summu yiino takise bikka xeise wora noosi. Hattonni
   c) Jirote anna ikkino takisete baataanchini baatama noosi takise jirosi hiro eonni xe’e ofolla noo woxi bikkinni likkenni gilletenni xa’mamaancho ikkanno.
4. Konni quwi cinaanchu quwi (3) wodho adhawoohu konni quwi cinaanchu quwi (2) baantay gede xa’minoonni takise balaxisiisatenni aante noo baatooshshuwa gumulate dihoolawo፡-
   a) Konni quwi cinaanchu quwi (2) qumminsoonni egensiishshira la’noonni woxi seerunni balaxote qoosso noo asale,
   b) Adhawoohunnita barru hoshsho lendeenna adhawoohu adhasi dandoonni fushshawo fulo,
5. Lamunna hakkuyi ale ikkitewo mannooti mitto

የተገለፀው የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለተረካቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

3. የዚህ አንቀጽንዑስ አንቀጽ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተረካቢው
   ሀ) ከባለሥልጣኑ አስቀድሞ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በእጁ የሚገኘውን የታክስ ከፋዩን ሀብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ማስታወቂያ ሳይደርሰው ወይም ማስታወቂያ ሳይሰጠው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የ30 (የሰላሳ) ቀናት ጊዜ ከማለፍ በፊት መሸጥ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ማስተላለፍ አይችልም፡፡
   ለ) ከሀብቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የገለጸውን የታክስ መጠን ወይም ባለሥልጣኑ የተስማማበትን የታክስ መጠን ቀንሶ ማስቀመጥ አለበት፡፡ እንዲሁም
   ሐ) የሀብቱ ባለቤት በሆነው ታክስ ከፋይ መክፈል ላለበት ታክስ ከሀብቱ ሽያጭ ገቢ ተቀንሶ መቀመጥ ባለበት የገንዘብ መጠን ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ ተረካቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እንዲከፍል ከተጠየቀው ታክስ በማስቀደም የሚከተሉትን ክፍያዎች ከመፈፀም አይከለክለውም፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው ማስታወቂያ ከተመለከተው ገንዘብ በሕግ የቅድሚያ መብት ያለውን ዕዳ፣
   ለ) የተረካቢውን አበል ጨምሮ ተረካቢው በተረካቢነት ችሎታው የሚያወጣቸውን ወጪዎች፣
5. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አንድን ታክስ ከፋይ በተመለከተ ተረካቢ

takise baataancho lainohunni tarakkaawoota ikkitawo yanna konni quwira la'noonni gadachuwanna hadari lamunku tarakkaawooti aana mittimmatena addinni gumulo ikkitawooha ikkanna gadachuwa lamunkuyi mittu tarakkaawichinni gumulantarara dandiitanno.

6. Konni quwi alaamira "adhawoho" yaa Itiyophiyu giddo afamanno takisete baataaanchi woy reenohu takise baataanchi jiro lainohunni aante noorinni mitto manchooti፡-
   a) Kubbaaniyyu buuxaancho
   b) Yoote mini woy yoote mini gobbaa mootoo'mino terekkaawichi
   c) Kassarino manchi yawo adhinohu
   d) Amadate uyinoonni jajja amadosi woroo assino manchi,
   e) Reenohu jiro buuxanno raggete buuxaanchi

41. Jiro Amada

1. Konni quwi cinaancho quwi (2) wodho noo gedeenni heedheenna, biilloonyu takisete baatooshshi yanna baatinokki takisete baataanchira hasiisannohu takisete qorowishshi iillisinku 30 (sajjuu) barri giddo baata hoogiro takisete baataanchi jiro amadantawo gede hajajo (''amadate hajajo'' yine qumminsanni) uyinannita ikka xawisanno qorowishsha takisete baataanchira aara dandaanno.
2. Biilloonyu takisete baataanchi hasamanno takise baatannoha ikkasihuluullo heera buuxiro amadamate hajajo hakkawoyintenni aara dandaanno.
3. Takisete baataanchi konni quwi cinaanchu quwi

በሚሆኑበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በሁለቱም ተረካቢዎች ላይ በአንድነትና በነጠላ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሲሆን፤ ግዴታዎቹ ከሁለቱ በአንዱ ተረካቢ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡

6. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ተረካቢ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የታክስ ከፋይንወይም የሚች ታክስ ከፋይን ሀብት በተመለከተ ከሚከተሉት አንዱ ሰው ነው፡-
   ሀ) የኩባንያ አጣሪ፣ ለ) በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ የተሾመ ተረካቢ፤
   ሐ) የከሰረ ሰው ባለአደራ፣
   መ) በመያዣ የተሰጠን ንብረት በይዞታው ሥር ያደረገ ሰው፤
   ሠ) የሚችን ሀብት የሚያጣራ ውርስ አጣሪ፤

41. ሀብትን ስለመያዝ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ላልከፈለ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ካልከፈለ የታክስ ከፋዩ ሀብት እንዲያዝ ትዕዛዝ ("የመያዣ ትዕዛዝ" ተብሎ የሚጠቀስ) የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ የሚከፍል ለመሆኑ ስጋት መኖሩን ካረጋገጠ የመያዣ ትዕዛዙን ወዲያውኑ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)

(1) uyinoonni qorowishshira worronni yanna giddo takise baata hoogiro woyi konni quwi cinaanchu quwi (2) la'noonnihu heera buuxiro biiilloonyu amadamate hajajo takisete baataanchira aara woy takisete baataanchi jiro amadosi woroo assino ayee manchi aana sayisara dandaanno.

4. Amadate hajajo konni woroonni tittirroonniri gobbaanni ayee takisete baataanchi jiro aana gumulo ikkitara dandiitanno.
   a) Jirosi aana balaxote qoosso noonsa woxu xa'miraanonni amadamino jaajji,
   b) Ayee yoote harinsho ittishsha assinoonni woy gumulote hajajo uyinoonni jajji,
   c) Itiyophiyu seeri garinni ittisamara dandaamannokki jajji,
5. Takisete baataanchi jajji aana amadamate hajajo uuyiniro woy uyinanniha ikkiro biiilloonyu borrotenni uyinanni egensiishshinni hajajanno jiro lainohunni tajimmatenni agalaggaltara dandiitanno ayee sanadeno woy xawishsha amadino ayee manchi tenne sanade woy xawishsha biiilloonyeho shiqishanno gede xa'mara dandaanno.
6. Amadamate hajajo garinni jajju amadamanno yanna poolisete mokkonnine bayichoho afamanno gede biiilloonyu hajajo aa dandaannoha ikkanna amadaminno jajji keeraanchimma garunni ofollanno gede assa noosi.
7. Biiilloonyu konni quwi garinni takisete baataanchi jajja amadanno yanna aante noo bixxilluwa amadino egensiishsha takisete baataanchira aanno፡-

በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ካልከፈለ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው መኖሩ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዙን ለታክስ ከፋዩ ሊሰጥ ወይም የታክስ ከፋዩን ሀብት በይዞታው ሥር ባደረገ በማንኛውም ሰው ላይ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

4. የመያዣ ትዕዛዙ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በማንኛውም የታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፡፡
   ሀ) በሀብቱ ላይ የቀደምትነት መብት ባላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች በተያዘ ንብረት፣
   ለ) በማናቸውም የፍርድ ሂደት ዕገዳ በተደረገበት ወይም የአፈፃፀም ትአዛዝ በተሰጠበት ንብረት፣
   ሐ) በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት፣
5. በታክስ ከፋዩ ንብረት ላይ የመያዣ ትዕዛዝ ከተሰጠ ወይም የሚሰጥ ከሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የሚያዘውን ሀብት በሚመለከት በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል ማንኛውንም ሰነድ ወይም መግለጫ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህን ሰነድ ወይም መግለጫ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡
6. በመያዣ ትዕዛዙ መሠረት ንብረት በሚያዝበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የተያዘውም ንብረት ደህንነቱ በሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት፡፡
7. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የታክስ ከፋዩን ንብረት በሚይዝበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል፡-
   ሀ) የተያዘውን ንብረት እና ያልተከፈለውን የታክስ መጠን፣

a) Amadamino jajjanna baantoonnikki takise bikka,
b) Takisete baataanchi egensiishshaho xawinsoonni jirosi amadante keeshshitanno yanna giddo hasi'nanni takise baatannokkiha ikkiro jirosi hiranno gede,

8. Konni quwi cinaanchu quwi (4) (A) wodho gumulora yine "jiro amadante keeshshitanno yanna" yaa
a) Balaashsha''anno udiinnichira udiinnu gara hedote giddora eessatenni biilloonyu ikkadoho yee wossananno yannaati.
b) Wolu ayee garinni uduunnu amadami gedenso noo tonne barruwa yannaati.

9. Takisete baataanchi konni quwi cinaanchu quwi (7) garinni uyinanni egensiishshira la'noonni baantoonnikki takise jajju amadame keeshshanno yanna goofimarchu barri geeshsha baatinokkiha ikkiro, biilloonyu jiro xawoho caratunni hiratenni hirotenni afamanno woxe aantete garinni aane noo baatooshshira hosanno gede assanno,
a) Umi deerrinni biilloonyunni wossanamanno bikkinni jirosi amadate, agaratenna hirate fultino fulo shaffanate,
b) Konni quwi cinaanchu quwi (7) uyinoonni egensiishshira la'noonni baantoonnikki takisete asale baatate,
c) Takisete baataanchi wole takisete asale baatate,
d) Konni quwi cinaanchu quwi 10 wodho noo gedeenni heedheenna, hirotenni anfonni woxi aaninni gatino womaashshi heeriro jajju hirami barrinni hanafe noo

ለ) ታክስ ከፋዩ በማስታወቂያው በተገለጸው ሀብቱ ተይዞ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ሀብቱን እንደሚሸጠው፤

8. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) (ሀ) ድንጋጌ አፈጻፀም ሲባል "ሀብት ተይዞ የሚቆይበት ጊዜ" ማለት፤
ሀ) ለሚበላሹ ዕቃዎች የዕቃዎቹን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ባለሥልጣኑ በቂ ነው ብሎ የሚወስነው ጊዜ፣
ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃዎቹ ከተያዙ በኋላ ያለው የአስር ቀናት ጊዜ ነው፡፡

9. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት በሚሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተውን ያልተከፈለ ታክስ ንብረቱ ተይዞ እስከ ሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻው ቀን ድረስ ያልከፈለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ሀብቱን በግልጽ ጨረታ በመሸጥ ከሽያጩ የሚገኘው ገንዘብ በቅደም ተከተል ለሚከተሉት ክፍያዎች እንዲውል ያደርጋል፣
ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ በባለሥልጣኑ በሚወሰነው መጠን ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለመሸጥ የወጣውን ወጭ ለመሸፈን፣
ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) በተሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተውን ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፣
ሐ) የታክስ ከፋዩን ሌላ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፣
መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ቀሪ ገንዘብ ካለ ንብረቱ ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ ለታክስ

45 barruwa giddo takisete baataanchira baatanno.

10. Takisete baataanchi borrotenni summeenyasi xawisiro konni quwi cinaanchu quwi 9 (D) la'noonni womaashsha albillitte daanno ayee takisete asale baatamate hosanna gede assa dandiinanni.
11. Konni quwi cinaanchu quwi (9) la'noonni garinni jiro hirreenna afamanno womaashshi takisete baataanchi hasamanno takisete asalenna jirosi amadate, agaratenna hirate fultewo fulonni ajannoha ikkanno yannara biilloonyu konni lallawi gafi garinni gatino asale baatisiisara dandaanno.
12. Biilloonyuni amadate hajajo sayinsoonni jiro amadino ayee manchino tenne jiro uyinokki woy aate umosi fajjikki gatinoha ikkiro konni quwi cinaanchu quwi 9 (A) garinni gumullanni fulo lendeenna uyinokki jiro waaga saikki takisete baataanchiwiinni hasi'nanni takise bikka gilletenni xa'mamaancho ikkanno.
13. Konni quwi garinni amadate hajajo aate dandiinannihu qaru dayrekiterchi woy konni loosira qaru dayrekiterchnni riqiwo uyinoonni takisete loosaasincho ikkanno.
14. Konni quwi garinni amadantino jiro biilloonyunni hajajantannonna biilloonyu halafinati woroo keeshshitannoha ikkanna ayee dani alaamira yine wolu ayii mootimmate loosi minira sae aamamara didandaanno.
15. Konni quwi garinni giwiru baataanchi jiro amadate dandaamannohu hasi'nanni giwiri ledo taalo ikkino bikkiniiti.

42. Faynaansete Uurrinshubbara Ofollino

ከፋዩ ይከፈለዋል፡፡

10. ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 9 (መ) የተመለከተው ገንዘብ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት እንዲውል ማድረግ ይቻላል፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) በተመለከተው መሠረት ከሀብት ሽያጭ የሚገኘውገንዘብ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት የታክስ ዕዳ እና ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅ እና ለመሸጥ ከወጣው ወጭ ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በዚህ የአዋጅ ክፍል መሠረት ቀሪውን ዕዳ ለማስከፈል ይችላል፡፡
12. በባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ሀብት የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ሀብት ያላስረከበ ወይም ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 (ሀ) መሠረት የሚወሰነውን ወጪ ጨምሮ ካላስረከበው ሀብት ዋጋ ሳያልፍ ከታክስ ከፋዩ ለሚፈለገው ታክስ መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
13. በዚህ አንቀጽ መሠረት የመያዣ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችለው ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ለዚሁ ተግባር በዋና ዳይሬክተሩ ውክልና የተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ይሆናል፡፡
14. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተያዘ ሀብት በባለሥልጣኑ የሚያዝና በባለሥልጣኑ ኃላፊነት ስር የሚቆይ ሲሆን ለምንም ዓይነት ዓላማ ተብሎ ለሌላ ለማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተላልፎ ሊሰጥ አይችልም፡፡
15. በዚህ አንቀጽ መሠረት የግብር ከፋዩን ሀብት ለመያዝ የሚቻለው ከሚፈለግበት ግብር ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መጠን ነው፡፡

Womaashshanna Jajja Amade Keeshshiisha

1. Kuni quwi jeefamannohu biilloonyu ikkadu korkaattinni takisete baataanchi aaninni hasiranno takise gamba assannoha ikkanna huluulo heedhusironna takise wiinamunni gamba yaa hasiissannota ikkiturooti.
2. Kuni quwi jeefamanno yannara biilloonyu mitte faynaansete uurrinshara aane noore jeefanno gede gashshootu hajajo aara dandaanno.
    a) Takisete baataanchi hisaawe milli yitawookki gede assara,
    b) Faynaansete uurrinsha giddo noo qorowishshunni amandanni udiinne worranni saaxine giddo ofollino ayee takisete baataanchi woxi, wuddete udiinni, ayirritino gexa gexe,woy wolu jajji milli yaannokki gede,
    c) Qorowishshunni amadamanno udiinne worranni saaxine giddo afantanno jiro gari taje woy saaxinete giddo noo jiro tittiro biilloonyeho aanno gede,
3. Konni quwi cinaanchu quwi (2) garinni fayinaansete uurrinshara uyinanni hajajo, hajajo jeefantanoha takisete baataanchi su’ma, teessonna takisete baataanchi badooshsshi kiiro amada noosi.
4. Konni quwi cinaanchu quwi (2) garinni hajajo uyinanni yanna, biilloonyu takisete dironna ayee albiidi takisete diro takisete baataanchi baatara hasiisanno takse lainohunni hakkawoyinte huluulote takise shallago loosara dandaanno.
5. Biilloonyu fayinaansete uurrinshara ittisate

42. በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ስለማቆየት

1. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው ባለሥልጣኑ በበቂ ምክንያት ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው ታክስ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ስጋት ሲኖረውና ታክሱ በአስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን ነው፡፡
2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ አንድ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን እንዲፈጽም አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
    ሀ) የታክስ ከፋዩ ሂሳቦች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲያደርግ፣
    ለ) በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ባለ በጥንቃቄ የሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠ ማንኛውም የታክስ ከፋዩ ጥሬ ገንዘብ፣ውድ ዕቃ፣የከበረ ጌጣጌጥ፣ወይም ሌላ ንብረት እንዳይንቀሳቀስ፣
    ሐ) በጥንቃቄ በሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ ስለሚገኙ ሀብቶች ተገቢውን መረጃ ወይም በሣጥኑ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ዝርዝር ለባለሥልጣኑ እንዲሰጥ፣
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ለፋይናንስ ተቋም የሚሰጠው ትእዛዝ ትእዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን የታክስ ከፋዩን ስም፣ አድራሻ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ በታክስ ዓመቱ እና በማናቸውም በቀደመው የታክስ ዓመት ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አስመልክቶ ወዲያውኑ የስጋት የታክስ ስሌት ሊያከናውን ይችላል፡፡

hajajo iillitunku 10 (tonnu) barruwa yanna giddo hajajo harunsitannota assate dandiisiisanno yoote mini fajjo afira noosi.

6. Itishshu hajajo uyini barrinni hanafe 10 barruwa yanna giddo yoote mini fajjo afira hoogguro biilloonyu uyiino hajajo jeefishshu uurrisanno.
7. Konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni hajajo iillitinose fayinaansete uurrinsha hajajo iillitu barrinni hanafe hajajote yanna gooffa geeshsha woy konni quwi cinaanchu quwi 6 garinni hajajote jeefishshi gooffa geeshsha hajajosi ayirrisa noosi.
8. Mitte womaashshu uurrinsha ikkado ikkinokki korkaattinni konni quwi cinaanchu quwi (2) uyinoonni hajajo garinni jeefikkinni gatinoha ikkiro hajajote la'noonni woxu bikkira hallanunni xa'mamannoha ikkanno.

43. Baantoonnikki Takise Sayikki Woganewiinni Baatisiisa

1. Mittu takisete baataanchi hasi'nanni takise baantanni yanna baatikki gatinoha ikkiro biilloonyu takisete baataanchira woxe baatanno sayikki bisira borrotenni aanno hajajonn ("baatooshshu hajajo yine" xawinsanniha) hajajote la'noonni woxe biilloonyeho baatanno gede hajajo aa dandaannoha ikkanna konni daninni baantanni woxi baantoonnikki takisete asale roora dinosi.
2. Baatooshshu hajajo takisete baataanchira woxe baatanno sayikki bisi damoozunni woy bikkaminno yannate danninni baantanni wole lawanno baatooshshi aaninni xeise eo assanno

5. ባለሥልጣኑ ለፋይናንስ ተቋሙ የዕግድ ትዕዛዝ በደረሰው በ10 (አሥር) ቀናት ጊዜ ውስጥ ትዕዛዙ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
6. የዕግድ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤት ፈቃድ ካልተገኘ ባለሥልጣኑ የሰጠው ትዕዛዝ ተፈጻሚነት ያቆማል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ትእዛዝ የደረሰው የፋይናንስ ተቋም ትእዛዙ ከደረሰው ቀን ጀምሮ የትእዛዙ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ወይም በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 መሠረት የትዕዛዙ ተፈጻሚነት እስከሚያበቃ ድረስ ትእዛዙን ማክበር ይኖርበታል፡፡
8. አንድ የገንዘብ ተቋም ያለ ምንም በቂ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሣይፈፅም የቀረ እንደሆነ በትዕዛዙ ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

43. ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል

1. አንድ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ ለሚከፍል ሦስተኛ ወገን በጽሑፍ በሚሰጥ ትዕዛዝ ("የክፍያ ትእዛዝ ተብሎ" የሚጠቀስ) በትዕዛዙ የተመለከተውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ እንዲከፍል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን በዚህ ዓይነት የሚከፈለው ገንዘብ ካልተከፈለው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም፡፡
2. የክፍያ ትዕዛዙ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ የሚከፍል ሦስተኛ ወገን ከደመወዝ ወይም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሚከፈል ሌላ ተመሳሳይ ክፍያ ላይ ቀንሶ ገቢ እንዲያደርግ

gede ikkanno yanna mittu mittunku baatooshshi aaninni xeanno woxu bikki baantanni damoozi woy wole baatooshshe ikkanna eote giwire xeinsi gedenonni mitto sayikkiha roora dinosi.

3. gutunni fannoonni Baanke hisaawe giddo afamanno woxe lainohunni baatooshshu hajajo baatannohura uyinannihu:-
   a) Baalunku gutu hisaawe annuwi baantoonnikki takisete asali heerinsaro woy
   b) Summumete maamari hisaawe lendikki, takisete baataanchi wolootu hisaawete annuwi malaati woy fajjo hasiissukkinni hisaawete aaninni woxe fushsha dandaannoha ikkiro callaati.
4. Baatooshshu hajajo garinni baatooshshe jeefanno ayee manchino hajajote la'noonni barra baatooshshe jeefa noosiha ikkanna, kunni barrino woxu baataanchi takisete baataanchira woxe baatara hasiisanno barri albaanni woy woxu takisete baataanchi su'minni amadami barri albaanni ikkara didandaanno.
5. Baatooshshu hajajo jeefate didandoommo yaanno woxu baataanchi baatooshshu hajajo iillitusi lamala barrubba giddo hajajo jeefate dandiinokki korkaatta biillonyeho borrotenni egensiisa noosi.
6. Woxu baataanchi konni quwi cinaanchu quwi (5) garinni biilloonyeho egensiishsha soyinoha ikkiro biilloonyu borrotenni qixxaawino egensiishshira ፡-
   a) Egensiishsha adhatenni baatooshshu

በሚሆንበት ጊዜ ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ የሚቀነሰው የገንዘብ መጠን ከሚከፈለው ደመወዝ ወይም ሌላ ክፍያ ሲሆን የገቢ ግብር ከተቀነሰ በኋላ አንድ-ሶስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

3. በጋራ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገኘን ገንዘብ በተመለከተ የክፍያ ትእዛዝ ለከፋዩ የሚሰጠው፡-
   ሀ) ሁሉም የጋራ ሂሳቡ ባለቤቶች ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ሲኖርባቸው፣ ወይም
   ለ) የሽርክና ማህበር ሂሳብን ሳይጨምር፣ ታክስ ከፋዩ የሌሎቹ የሂሳብ ባለቤቶች ፊርማ ወይም ፈቃድ ሳያስፈልገው ከሂሳቡ ላይ ገንዘብ ማውጣት የሚችል ሲሆን ብቻ ነው፡፡
4. በክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ክፍያ የሚፈፅም ማናቸውም ሰው በትዕዛዙ በተመለከተው ቀን ክፍያውን መፈፀም ያለበት ሲሆን፣ ይህም ቀን ገንዘብ ከፋዩ ለታክስ ከፋዩ ገንዘቡን ሊከፍል ከሚገባበት ቀን በፊት ወይም ገንዘቡ በታክስ ከፋዩ ስም ከተያዘበት ቀን በፊት ሊሆን አይችልም፡፡
5. የክፍያ ትዕዛዙን ለመፈፀም አልቻልኩም የሚል ገንዘብ ከፋይ የክፍያ ትዕዛዙ በደረሰው በሰባት ቀናት ውስጥ ትዕዛዙን ለመፈፀም ያልቻለበትን ምክንያት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡
6. ገንዘብ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ለባለሥልጣኑ ማስታወቂያ የላከ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በተዘጋጀ ማስታወቂያ፡-
   ሀ) ማስታወቂያውን በመቀበል የክፍያ ትዕዛዙን ሊሰርዘው ወይም

hajajo rige hunara woy woyyeessara woy

b) Woxu baataanchira sonkoonnisi egensiishsha tuge hunara dandaanno.

7. Takisete baataanchi hansannisi takise wo'munni woy bocunni baatinoha woy takise bantanni gara biilloonyunniwa adhamooshshu noo baatooshshu summummenni jeefinsoonniha ikkiro biilloonyu baataanchoho sayise noo baatooshshu hajajo borrotenni uyinoonni egensiishshinni agurara woy woyyeessara dandaanno.

8. Biilloonyu konni quwi garinni baataanchoho aanno hajajo woy egensiishshu affino takisete baataanchira sowa noosi.

9. Biilloonyu baataanchunni baatamino ayee woxeno takisete baataanchi hasamanno takisete asali aaninni xeisanno.

10. Konni quwira uyinanni egensiishsha mittu ikkadu korkaatti nookkiha adhinokki manchi egensiishshaho la'noonni woxu bikka halanyunni xa'mamannoha ikkanno.

11. Kuni quwi Itiyophiyu seeri garinni ittisa dandiinannikki jajji aana jeefamara didandaanno.

12. Konni quwi jeefishshira "baataanchu" yaa፡

a) Takisete baataanchira asalaancho ikkino woy albillitte asalaancho ikkannohu,

b) Takisete baataanchira woy takisete baataanchi su'minni woxe amadino woy albillitte amadannohu,

c) Takisete baataanchira baantanni wolu manchi woxe amadinohu,

d) Takisete baataanchira woxe baantanni gede

ሊያሻሽለው ወይም

ለ) ለገንዘብ ከፋዩ የተላከለትን ማስታወቂያ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

7. ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ ወይም ስለታክስ አከፋፈሉ በባለሥልጣኑን ዘንድ ተቀባይነት ያለው የክፍያ ስምምነት የፈፀመ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለከፋዩ አስተላልፎት የነበረውን የክፍያ ትእዛዝ በጽሑፍ በተሰጠ ማስታወቂያ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

8. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለከፋዩ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ማስታወቂያ ግልባጭ ለታክስ ከፋዩ መላክ አለበት፡፡

9. ባለሥልጣኑ በከፋዩ የተከፈለውን ማንኛውንም ገንዘብ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት የታክስ ዕዳ ላይ ያቀናንሳል፡፡

10. በዚህ አንቀጽ የሚሰጠውን ማስታወቂያ ያለምንም በቂ ምክንያት ያልተቀበለ ሰው በማስታወቂያው ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

11. ይህ አንቀጽ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡

12. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ከፋይ" ማለት፡

ሀ) ለታክስ ከፋዩ ባለዕዳ የሆነ ወይም ወደፊት ባለዕዳ የሚሆን፤

ለ) ለታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም ገንዘብ የያዘ ወይም ወደፊት የሚይዝ፤

ሐ) ለታክስ ከፋዩ የሚከፈል የሌላ ሰው ገንዘብ የያዘ፤

wolu manchinni fajjo uyinoonni manchooti.

44. Gobbatenni Fula Hoolate Uyinanni Hajajo.

1. Konni quwi woro jeefantannohu biilloonyu takisete baataanchi woy uurrinshate loosu harisaanchi woy mittu kubbaaniyyiira rooridi qeechi noosi miili aane noo baatooshshe baatikki gobbateyi fulara dandaanno yaannohu ikkadu korkaatti heerisiro ikkanno.
   a) Takisete baataanchinni baatama hasiissannosi woy albillite baantanni takise woy;
   b) Takisete baataanchi gumulo aate widoonni rooridi qeechi noo kubbaaniyyi baata noosi woy albillitte baantanni takise,
2. Konni quwira la'noonni ikkitibba xaaduro biilloonyu takisete baataanchi aante noorinni mitto jeefasira albaanni Itiyophiyunni fulawokki gede hooltanno hajajo "gobbateyi fula hooltanno hajajo" yine xawinsannita aara dandaanno.
   a) Takisete baataanchinni woy takisete baataanchi gumulo aate widoonni rooridi qeechi noosi kubbaaniyyi baantantara hasiisanno woy albillitte baatanno takise wo'munni baata geeshsha,
   b) Biilloonyu adhanno garinni takisete baataanchi konni quwi cinaanchu quwi (A) la'noonni takise baatate baatooshshu summuume assiro.
3. Gobbatenni fulannookki gede hooltanno hajajo aane noore amada heedhannose ፡-
   a) Hajajo jeefanttanno takisete baataanchi su'ma teessonna takisete baataanchi badooshshi kiiro

መ) ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ እንዲከፍል በሌላ ሰው ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

44. ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ወይም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በአንድ ኩባንያ አብላጫ ድርሻ ያለው አባል የሚከተሉትን ክፍያዎች ሳይከፍል ከሀገር ሊወጣ ይችላል የሚል በቂ ምክንያት ሲኖረው ይሆናል፡፡
   ሀ) በታክስ ከፋዩ መክፈል የሚኖርበትን ወይም ወደፊት የሚከፈል ታክስ፣ወይም
   ለ) ታክስ ከፋዩ ውሳኔ በመስጠት ረገድ አብላጫ ድርሻ ያለው ኩባንያ መክፈል የሚኖርበትን ወይም ለወደፊቱ የሚከፈል ታክስ፣
2. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ከሚከተሉት አንዱን ከመፈፀሙ በፊት ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ የሚከለክል ትእዛዝ "ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ" ተብሎ የሚጠቀስ ሊሰጥ ይችላል፡፡
   ሀ) በታክስ ከፋዩ ወይም ታክስ ከፋዩ ውሳኔ በመስጠት ረገድ አብላጫ ድርሻ ባለው ኩባንያ ሊከፈል የሚገባው ወይም ወደፊት የሚከፈለው ታክስ በሙሉ እስከሚከፈል፣
   ለ) ባለሥልጣኑ በሚቀበለው አኳኋን ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከተውን ታክስ ለመክፈል የክፍያ ስምምነት ሲያደርግ፤
3. ከሀገር እንዳይወጣ የሚከለክለው ትዕዛዝ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-
   ሀ) ትዕዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ታክስ

b) Gobbatenni fulannokki gede hoolloonni manchi, uurrishsha woyi kubbaaniyyi baata hasiissanno woy albillitte baata hasiissannosiha takisete bikka,

4. Biilloonyu shiqishanno ku’laato garinni biilloonyu noosi yoote mini seedisa hoogiro konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni sa’anno gobbatenni fula hooltanno hajajo, hajajo uyiini yannanni hanafe 10 (tonne) barruwa gedeno dijeefamanno.

5. Biilloonyu takisete baataanchi gobbatenni fulannokki gede hooltanno hajaajo affino xawinsoonni takise baataanchira aa noosiha ikkanna takisete baataanchi hajajo adha hooga konni quwi garinni assinanni ayee assoteno jeefamannokki gede diassanno.

6. Immegireeshiinetenna dehininnetete biilloonyi sooreessi hoolate hajajo iillitusiro hajajo loosu aana hosiisate hasiissanno qaafubba adhanno, sooreessu adhanno qaafubba ayee paspoorteno, ayimmate kaarde woy wole takisete baataanchi Itiyophiya agure fulate horoonsiranno ayee sanadeno amadanna worano ledanno.

7. Woloota immegireeshiinete balaxo ikkito wo’ma noo gedeenni heedheenna, takisete baataanchi gobba agure fulannokki gede uyinoonni hajajo aana la’noonni takise baatiro woy takise baatanno gede biilloonyunniwa adhamooshshu noo baatooshshu summume jeefiro biilloonyu takisete baataanchira gobbatenni fulate dandiissiisanno afanshu woraqata aannosi. Takisete baataanchi konne afanshu woraqata shiqishasi takisete baataanchi Itiyophiyunni fulanno gede fajjate

ከፋይ ስም፣ አድራሻ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፤

ለ) ከሀገር እንዳይወጣ የተከለከለው ሰው፣ ድርጅት ወይም ኩባንያ ሊከፍል የሚገባውን ወይም ለወደፊቱ ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን፤

4. ባለሥልጣኑ በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ካላራዘመው በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚተላለፈው ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከ10 (አስር) ቀናት በኋላ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5. ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ከሀገር እንዳይወጣ የሚከለክለውን ትዕዛዝ ግልባጭ ለተጠቀሰው ታክስ ከፋይ መስጠት የሚኖርበት ሲሆን የታክስ ከፋዩ ትዕዛዙን አለመቀበል በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከናወነውን ማንኛውንም ተግባር ተፈፃሚ እንዳይሆን አያደርገውም፡፡

6. የኢሚግሬሽንና ደህንነት ባለሥልጣን ኃላፊ የክልከላ ትዕዛዙ ሲደርሰው ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ኃላፊው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ማንኛውንም ፓስፖርት፣ መታወቂያ ወይም ሌላ ታክስ ከፋዩ ኢትዮጵያን ለቆ ለመውጣት የሚጠቀምበትን ማንኛውንም ሰነድ መያዝና ማስቀመጥን ይጨምራል፡፡

7. ሌሎች የኢሚግሬሽን ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ታክስ ከፋዩ ሀገር ለቆ እንዳይወጣ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተመለከተውን ታክስ ከከፈለ ወይም ታክሱን እንደሚከፍል በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያለውን የክፍያ ስምምነት

immegireshiinete loosaasinchira ikkado taje ikkannosi.

8. Konni quwi garinni seeraame ikkitinno dogonni loosantino ayee assoti korkaattinni moottimmate woyi takisete, gumurukete, immegireeshiinete, poolisete woy wolu loosaasinchi aana ayee dani jaddo woy fitihaberete kisse shiqa woy sufantara didandiitanno.
9. Gobbatenni fula hooltanno hajajo uyinara dandiinannihu qaru dayrekiterchinni woy tenne hajajo aano gede qaru dayrekiterchi riqiwinno loosaasinchooti.

45. Daddalu Uurrinsha Yannate Geeshshira cufa (Ashshaga)

1. Konni quwi woro jeefanttannohu mittu takisete baataanchi wirro wirro፡-
   a) Giwiru seeri garinni hasi'nanni sanade amadikki gatiro woy
   b) Takise baantanni yanna baatikki gatiro ikkanno.
2. Konni quwi woro jeefantanno yanna takisete baataanchi qorowishshu iillisinku 7 barruwa giddo hasi'nanni ledote issete takise, ekisayizi takise woy baantanni hisaawe aaninni xeinse amadandanni takise baatinokkiha ikkiro woy hasi'nanni sanade amadinokkiha ikkiro biilloonyu takisete baataanchi daddalu uurrinsha 14 barrira yannate geeshshira cufannoha ikksi xawisanno borrote qorowishsha aanno.
3. Takisete baataanchi konni quwi cinaanchu quwi (2) uyinoonni qorowishshi garinni takise baata hoogiro woy hasi'nanni sanade amada

ከፈፀመ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ከሀገር ለመውጣት የሚያስችለው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ ታክስ ከፋዩ ይህንን የምስክር ወረቀት ማቅረቡ ታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ለመፍቀድ ለኢሚግሬሽን ሠራተኛ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሕጋዊ በሆነ መልኩ በተከናወነ ማንኛውም ተግባር ምክንያት በመንግሥት ወይም በታክስ፣ በጉምሩክ፣ በኢምግሬሽን፣ በፖሊስ ወይም በሌላ ሠራተኛ ላይ ምንም ዓይነት የወንጀል ወይም የፍትሐብሄር ክስ ሊቀርብ ወይም ሊቀጥል አይችልም፡፡
9. ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው በዋና ዳይሬክተሩ ወይም ይህንን ትእዛዝ እንዲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩ በወከለው ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡

45. የንግድ ድርጅትን ለጊዜው ስለማሸግ

1. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ታክስ ከፋይ በተደጋጋሚ፡-
   ሀ) በግብር ሕግ መሠረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይይዝ ሲቀር፣ ወይም
   ለ) ታክሱን በመክፍያ ጊዜው ሳይከፍል ሲቀር ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ7 (በሰባት) ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚያዘውን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን የንግድ ድርጅት ለ14 (ለአስራ አራት) ቀን በጊዜያዊነት የሚያሽግ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
3. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ታክሱን

hoogiro biilloonyu takisete baataanchi daddalu uurrinsha 14 barra roortinokki yanna bocunni woy wo'munni cufantanno gede assinanni hajajo ("cufate hajajo" yinne xawinsanni) hajajo aanno.

4. Biilloonyu hajajo loosu aana hosiissanno yannara takisete baataanchi daddalu uurrinsha ea dandaannoha ikkanna cufate hajajo loosu aana hosiissanno yannara polise bayichoho afantanno gede hajajo aara dandaanno.
5. Biilloonyu cufate hajajo garinni cunfoonni takisete baataanchi daddalu uurrinshsha ijaari aana albaanni leellanno bayicho aante noo qaala amadino egensiishsha xallanno.፦ "Takisete gadachuwa fula hogatenni qoqqowu takisete gashshooti lallawi quwa 45 garinni Sidaamu qoqqowi eote biilloonyi hajajonni yannate geeshshira cunfoonni".
6. Aante noo iikitubba wo'mite afanturo biilloonyu takisete baataanchi daddalu uurrinsha wirro fananni gede assanno፦
   a) Qaru dayrekiterchi woy riqiwo uyinoonni loosaasinchi takisete baataanchi hisaawete maareeko sanadda amadate dandiissiisanno ikkado qaafo adhino yee ammaniro,
   b) Takisete baataanchi takise baatannoha ikkiro
7. Cufate hajajo uyinannihu qaru dayrekiterchinni woy qole cufate hajajo aate baxxino garinni qaru dayrekiterchi riqiwo uyinoonni takisete loosaasinchinni callaati.

46. Sa'inori Takiste Asalla

1. Mittu takisete baataanchi ("sayisaanchu" yine

ካልከፈለ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ካልያዘ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት ከ14 (ከአስራ አራት) ቀን ላልበለጠ ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲታሸግ የሚያደርግ ትዕዛዝ ("የማሸጊያ ትዕዛዝ" ተብሎ የሚጠቀስ) ይሰጣል፡፡

4. ባለሥልጣኑ ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት መግባት የሚችል ሲሆን የማሸጊያ ትዕዛዙ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ፖሊስ በቦታው እንዲገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በማሸጊያ ትዕዛዝ መሠረት በታሸገው የታክስ ከፋዩ ንግድ ድርጅት ህንፃ ላይ ፊት ለፊት በሚታይ ቦታ የሚከተሉትን ቃላት የያዘ ማስታወቂያ ይለጥፋል፡- "የታክስ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፵፭ መሠረት በሲዳማ ክልል ገቢዎች ባለሥልጣን ትዕዛዝ ለጊዜው ታሽጓል"፡፡
6. የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት እንደገና እንዲከፈት ያደርጋል፡-
   ሀ) ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ዉክልና የተሰጠው ሠራተኛ ታክስ ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ሰነዶችን ለመያዝ የሚያስችል በቂ እርምጃ ወስዷል ብሎ ሲያምን፤
   ለ) ታክስ ከፋዩ ታክሱን የሚከፍል ከሆነ፣
7. የማሸጊያ ትዕዛዝ የሚሰጠው በዋና ዳይሬክተሩ ወይም ደግሞ የማሸጊያ ትእዛዝ ለመስጠት በልዩ ሁኔታ በዋና ዳይሬክተሩ ዉክልና በተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ብቻ

qumminsanni) harisanno daddalu loosi ledo xaadinohunni baantoonnikki takisete asali nooha ikkironna daddalu jiro wo'munni woy bocunni xaadooshshu noo manchira "jiro sa'inosi mancho" yine qumminsara sayisinoha ikkiro daddalu jiro ledo amadaminiha baantoonnikki asale jiro sa'inosi manchi baatate gadacho heedhannosi.

2. Konni quwi cinaanchu quwi (1) wodho biilloonyu sainoha takisete asale wo'muyi woy bocuyi jiro sayisaawohu aaninni xa'mawookki gede di'ittisawoosi.

47. Uurrinshatenni Baantanni Takise

1. Mitte uurrinsha takise baantanni yanna giddo baattinokkiha ikkiro takise baantoonnikki yanna woy takise baatamate albaanni noo lewu agani yanna giddo loosu harisaancho ikke noo ayee manchino baatantinokki takise uurrinshate ledo mittimmatenna addinni(naxalu)hadari heerannosi.
2. Koni quwi cinaanchu quwi (1) dingaage aane noorinni gumulo di'ikkanno.
   a) Uuurrinshate hasi'nanni giwire baattukki gatinohu konni quwi cinaanchu quwi (1) qumminsoonni manchi fajjonni woy egennote gobbaa ikkinoha ikkironna
   b) Loosu harisaanchira uyinoonni hadarinna wolootu huneeti leelliro loosu harisaanchi uurrinsha giwire baata hoogate assitanno sharro hoolate hasiisanno wo'naalsha leellishinoha ikkinoha ikkirooti.

48. Awaawurshu Woy Takisete Maaxooshshi Gumulamiro Heerannoha Takisete Qeecha

1. Farci'noonnisi odiiterchi, farci'noonnisi

ነው፡፡

46. የተላለፉ የታክስ ዕዳዎች

1. አንድ ታክስ ከፋይ ("አስተላላፊ" ተብሎ የሚጠቀስ) ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ ጋር በተገናኘ ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ያለበት እንደሆነ እና የንግዱን ሀብቶች በሙሉ ወይም በከፊል ግንኙነት ላለው ሰው "ሀብቱ የተላለፈለት ሰው" ተብሎ ሊጠቀስ ያስተላለፈ እንደሆነ ከንግዱ ሀብት ጋር ተያይዞ ያልተከፈለውን ዕዳ ሀብቱ የተላለፈለት ሰው የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ባለሥልጣኑ የተላለፈውን የታክስ ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ከሀብት አስተላላፊው ላይ እንዳይጠይቅ አያግደውም፡፡

47. በድርጅት ስለሚከፈል ታክስ

1. አንድ ድርጅት ታክሱን በመክፈያው ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ ታክሱ ባልተከፈለበት ጊዜ ወይም ታክሱ ከመከፈሉ በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሥራ አስኪያጅ የነበረ ማንኛውም ሰው ላልተከፈለው ታክስ ከድርጅቱ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፃሚ አይሆንም፤
   ሀ) ድርጅቱ የሚፈለግበትን ግብር ሳይከፍል የቀረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው ሰው ፈቃድ ወይም ዕውቀት ውጭ የሆነ እንደሆነ፣ እና
   ለ) ለሥራ አስኪያጅ የተሰጠው ኃላፊነት እና ሌሎች ሁኔታዎች ሲታዩ ሥራ አስኪያጁ ድርጅቱ ግብር ላለመክፈል የሚያደርገውን ጥረት ለመከላከል ተገቢውን ትጋት አሳይቶ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

pabilikete hisaawe ogeessi woy pabilikete odiiterchi

a) Takisete baataanchi takise ajishate woy takise maaxate dandaamanno gede kaa'linohu, jawaachishinohu, wo'naalinoha ikkiro,

b) Takise ajishate woy takise maaxate dandiissiisanno garinni ayee doogonnni afanni takisete baataanchi ledo halamiro woy assootu kaa'laancho ikkiro, takise awaawurate woy takisete loosisi korinni kalaqamanno takisete aja takisete baataanchi ledo mittimmatenninna addinni qeechu noosi.

2. Mittu farci'noonnisi odiiterchi,farci'noonnisi pabilikete hisaawete ogeessi, woy pabilikete odiiterchi konni quwi cinaanchu quwi (1) worroonni garinni halaafe ikke afamiro biilloonyu konne assoote ፡-

a) Farci'noonninsa pabilikete hisaawe ogeeyye uurrinsha, Tophiyaho hisaawetenna odiitete boorde woy konni manchi fajjo aanno bisi ripoorte assa noosiha ikkanna boordeno odiiterchu fajjo rigge huntanno gede xa'mitanno woy

b) Daddalu fajjo aate halafinnatinoose biilto ripoorte assanno.

3. 3.Konni quwira "takise ajisha" yaanno handaari konni lallawi quwira 103 uyinoonni tiro heedhanno.

Gafa Sette

Kiiso, Wirri Qolonna Takisete Asalinni Coicha/ Natsa/ Ikkannire

49. Takisete Baatooshshira Uyinanni Kiiso

48. ማጭበርበር ወይም የታክስ ስወራ ሲፈፀም ስለሚኖር የታክስ ኃላፊነት

1. የተመሰከረለት ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ፐብሊክ የሂሳብ ባለሙያ ወይም ፐብሊክ ኦዲተር

ሀ) ታክስ ከፋዩ ታክስን ለማሳነስ ወይም ታክሱን ለመሰወር እንዲችል የረዳ፣ ያበረታታ፣ የሞከረ እንደሆነ፣

ለ) ታክስ ለማሳነስ ወይም የታክስ ስወራን በሚያስከትል መልኩ በማንኛውም መንገድ እያወቀ ከታክስ ከፋዩ ጋር ከተባበረ ወይም የድርጊቱ አጋር ከሆነ በታክስ ማጭበርበሩ ወይም በታክስ ስወራው ምክንያት ለሚከሰተው የታክስ መቀነስ ከታክስ ከፋዩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

2. አንድ የተመሰከረለት ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ፐብሊክ የሂሳብ ባለሙያ ወይም ፐብሊክ ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ኃላፊ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ ይህንን ድርጊት፡-

ሀ) ለተመሰከረላቸው የፐብሊክ ሂሳብ ባለሙያዎች ተቋም፣ ለኢትዮጵያ የሂሳብና የኦዲት ቦርድ ወይም ለዚህ ሰው ፈቃድ ለሚሰጠው አካል ሪፖርት ማድረግ ያለበት ሲሆን ቦርዱም የኦዲተሩን ፈቃድ እንዲሰርዘው ይጠይቃል፣ ወይም

ለ) የንግድ ፈቃድ የመስጠት ኃለፊነት ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ "ታክስን ማሳነስ" የሚለው ሀረግ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 103 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

ክፍል ስምንት

1. Takisete baataanchi takisete diro baantanni hisaawe aaninni xeinse gatinsoonni takisenna balaxe baatino takisera afira hasiissannosi kiiso takisete baataanchi takisete diro hasamanno eote giwiri asali rooranno yanna, biilloonyu rooreenyunni leellino womaashsha aane noo garinni loosu aana hosanno gede assanno.
   A) Umihunni (baantanni hisaawe aaninni xe'e gattanno takise lendikki) takisete baataanchi eote giwiri lallawi garinni hasi'nannisi ayee takise baatate hosanno.
   B) Gattino takise baataanchu wole ayee takisete seerinni hasi'nanni takise baatate hosanno.
   C) Konni quwi cinaanchu quwi 2 noo gedeenni heereenna, tirfino woxi heeriro takisete baataanchi borrotenni wirro qolate xa'mo shiqishi barriyi hanafe noo 90 (honsawo) barruwa giddo takisete baataanchira wirro qollannisi.

2. Takisete baataanchi borrotenni summeenyasi xawisiro konni quwi cinaanchu quwi 1 (C) la'noonni woxe albillitte daanno ayee takisete asalira baatamanno gede tareessa/ashshagaaggarara dandaanno.
3. Biilloonyu konni quwi cinaanchu quwi 1 (C) worroonni garinni tirfino woxe takisete baataanchira baata hoogiro, honsawu barri goofihunni hanafe tirfete woxi higa barri geeshsha noo yanna giddo takisete baataanchi qallo afirate qoosso noosi.
4. Konni quwi cinaanchu quwi 3 garinni

ማካካሻ፣ ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን

49. ለታክስ ክፍያዎች የሚሰጥ ማካካሻ

1. ታክስ ከፋዩ በታክስ ዓመቱ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለቀረበት ታክስ እና በቅድሚያ ለከፈለው ታክስ ሊያገኝ የሚገባው ማካካሻ ታክስ ከፋዩ በታክስ ዓመቱ ከሚፈለግበት የገቢ ግብር ዕዳ በሚበልጥበት ጊዜ፤ ባለሥልጣኑ በብልጫ የታየውን ገንዘብ በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
   ሀ) በመጀመሪያ (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀርን ታክስ ሳይጨምር) ታክስ ከፋዩ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤
   ለ) ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል ይውላል፡፡
   ሐ) የዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተራፊ ገንዘብ ካለም ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡
2. ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) የተመለከተው ገንዘብ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) በተደነገገው መሠረትተራፊውን ገንዘብ ለታክስ ከፋዩ ካልከፈለ፤ ዘጠናው ቀን ካለቀ ጀምሮ ተራፊው ገንዘብ እስከሚመለስበት

baantanni qallo mixxaane cinaanchu quwira la’noonni yanna hanaffara shiimare balaxxe noo ruuwete diro daddalu baankuwara loosi aana hosino lowiidi liqoote qallo mixxaane ikkanno.

50. Baatama Hasiissannohu Alee Baatantino Takise Qolannire

1. Konni quwi cinaanchu quwi (2) wodho noo gedeenni heedheenna, takisete baataanchi (konni lallawi quwi 49 worroonnire lendikki) takisete seeri garinni baatara hasiisanno takise aleenni baatinoha ikkiro takise baatantu barrinnii hanafe noo sasu diri giddo tsaddaqantino qitse horoonsiratenni baatara hasiisannohu aleenni baatino takise higgawoosi gede biilloonyeho ku’lara dandaanno.
2. Kuni quwi gumulo ikkannohu takisete baataanchi baatara hasiisanno takise aleenni baatino takise lainohunni biilloonyu takisete shallago woyyo assanno gede gadachannosi richi nookkiha ikkino ikkirooti.
3. Biiloonyu ku’laatote aana uyinoonni gumulo konni quwi cinaanchu quwi (1) qummisino ku’laanchira borrotenni egensiisa noosi.
4. Tkisete baataanchi konni quwi cinaanchu quwi (1) garinni ku’lironna biilloonyu takisete baataancho takisete seeri garinni baatara hasiisannohu aleenni baatinoha ikka ammanisiro roorunni/bilcunni baantoonni woxi bikka aante noo aanta garinni loosu aana hosiisanno፡-
   a) Umo (baantanni hisaawe aaninni xeinseenna gattanno takise lendikki)

ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የማግኘት መብት አለው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ወለድ መጣኔ በንዑስ አንቀፁ የተመለከተው ጊዜ ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ብሎ ባለው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ የዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ይሆናል፡፡

50. ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለን ታክስ ስለመመለስ

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ታክስ ከፋዩ (በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 የተደነገገውን ሳይጨምር) በታክስ ሕግ መሠረት ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለ እንደሆነ ታክሱ ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለው ታክስ ይመለስለት ዘንድ ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለውን ታክስ በሚመለከት ባለሥልጣኑ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲያደርግ የሚያስገድደው ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ነው፡፡
3. ባለሥልጣኑ በማመልከቻው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሰው አመልካች በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡
4. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሲያመለክትና ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያምንበት በብልጫ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን

takisete baataanchi eote giwiri lallawi garinni hasi’nanni ayee takise baatate hosanno

b) Gattino takise baataanchi wole ayee takisete seerinni hasi’nanni takise baatate hosanno

c) Konni quwi cinaanchu quwi 5 noo gede heereenna, tirfete woxi heeriro takisete baataanchi wirro higate xa’mo shiqishiri barrinni hanafe noo 45 (shoyilliina onte) barruwa giddo takisete baataanchira qollannisi.

5. Takisete baataanchi borrotenni summeenyasi xawisiro konni quwi cinaanchu quwi 4 (C) la’noonni woxi ayee takisete seeri garinni albillitte daanno ayee takisete asali baatooshshira sa’’ara dandaanno.

6. Biilloonyu konni quwi garinni takise sorotenni qolinoha ikkiro takisete baataanchi biilloonyunni xa’mamiro xa’mamate sanadera qumminsoonni barra sorotenni higinosi woxe biilloonyeho wirro baata noosi.

7. Wirro qolate xa’mirinotakisete baataanchi sorisiishshini woxu sorotenni higinoha ikkiro takisete baataasinchi woxu sorotenni higino wotenna sorotenni higino woxe qole biiltote baatino barri mereero noo yanna konni lallawi quwa 37 (2) laino jilbi garinni baatooshshu keeshshino yanna qallo baatate gadacho noosi.

8. Takise baataanchi konni quwi cinaanchu quwi (7) baataawo gede gadachitanno wirro qolate takise konni lallawi gumulora yine takisete baataanchi baatawota ayee takise assine adhinanni.

በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ ያውላል፡-

ሀ) በመጀመሪያ (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀረውን ታክስ ሳይጨምር) ታክስ ከፋዩ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤

ለ) ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል ይውላል፡፡

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተራፊ ገንዘብ ካለ ታክስ ከፋዩ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 (አርባ አምስት) ቀናት ወስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡

5. ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4(ሐ) የተመለከተው ገንዘብ በማንኛውም የታክስ ሕግ መሠረት ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል፡፡

6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ታክስ በስህተት ተመላሽ ያደረገ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ በመጠየቂያ ሰነድ በተጠቀሰው ቀን በስህተት የተመለሰለትን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ መልሶ መክፈል አለበት፡፡

7. ተመላሽ በሚጠይቀው ታክስ ከፋይ አሳሳችነት ገንዘብ በስህተት የተመለሰ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ገንዘቡ በስህተት በተመለሰበትና በስህተት የተመለሰው ገንዘብ ተመልሶ ለባለሥልጣኑ በተከፈለበት ቀን መካከል ላለው ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 (2) በተመለከተው መጣኔ መሠረት ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

8. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) እንዲከፍለው የሚገደደው ተመላሽ ታክስ

51. Jawu Qarri Xaadiro Uynannita Takisete Maaro

1. Kuni quwi jeefamannohu. biirote sooreessi፡-
   a) hendoonnikki kalaqamu dano woy huno korinni woy takisete baataanchi de’nenni woy ayee huno ledo xaadinokki garinni kalaqamino lowo hallanyu qarri korkaatinni takisete baataanchi hasi’nanni takise wo’munni baatanno gede assa dandaannokki ayirrino qarra iillishannoha ikka woy
   b) Takisete baataanchi rewo korkaatinni takisete baataanchi baata noosi takise wo’ma baatawo gede assa takisete baataanchi irkiraano aana jawa qarra kalaqannoha ikkasi, ammanirooti.
2. Konni quwi cinaanchu quwi (3) noo gedeenni heereenna, kuni quwi gumulo afiriro biirote sooreessi takisete baataancho woy reenohu takise baataanchi jajja buuxannohu raggete buuxaanchi baatama noosi takisenna tenne takise ledo xaadino keeshshino baatooshshira xa’minanni qallo wo’munni woy bocunni baatannokki gede fajjara dandaanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi (1) garinni takisete asali maaro assa dandiinayihu gashshootu amaale mini fushshanno wodhonni gumullanni woxi bikki deerinni ikkanno.
4. Biirote sooreessi takisete baataancho woy reenohu jajja buuxanno raggete buuxaancho takisete asalinni natsa assitanno gumulo uyiinohu shiqqinosi awaawurshu woy sorote taje aana xintamatenni ikkiro maaro assineenna gatino takisete asali maaro aate

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ታክስ ከፋዩ እንደሚከፍለው ማንኛውም ታክስ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

51. ከባድ ችግር ሲያጋጥም ስለሚሰጥ የታክስ ምህረት

1. ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ የሚሆነው፣ የቢሮ ኃላፊው፡-
   ሀ) ባልተጠበቀ የተፈጥሮ አደጋ ወይም ጥፋት ምክንያት ወይም ከታክስ ከፋዩ ቸልተኝነት ወይም ማንኛውም ጥፋት ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ የተፈጠረ ከባድ የግል ችግር ምክንያት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ እንዲከፍል ማድረግ የማይቋቋመው ከባድ ችግር የሚያስከትልበት መሆኑን፤ ወይም
   ለ) በታክስ ከፋዩ ሞት ምክንያት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚኖርበትን ታክስ በሙሉ እንዲከፈል ማድረግ በታክስ ከፋዩ ጥገኞች ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥር መሆኑን፤ሲያምንበት ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ከሆነ የቢሮው ኃላፊው ታክስ ከፋዩ ወይም የሚቹን ታክስ ከፋይ ንብረት የሚያጣራው ውርስ አጣሪ መከፈል የሚኖርበትን ታክስና ከዚህ ታክስ ጋር በተገናኘ ለዘገየ ክፍያ የሚጠየቀውን ወለድ በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይከፈል ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የታክስ ዕዳ ምህረት ሊደረግ የሚችለው የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰን የገንዘብ መጠን ልክ ይሆናል፡፡
4. የቢሮው ኃላፊው ታክስ ከፋዩን ወይም የሚቹን ንብረት የሚያጣራውን ውርስ አጣሪ ከታክስ ዕዳ ነጻ የሚያደርገውን ውሳኔ የሰጠው በቀረበለት የተጭበረበረ

albaanni alba noo widira higatenni takisete baataanchi takisete asalinni natsa assinoonnikki gede kiirrena kuni lallawi jeefamano.

5. Biirote sooreessi konni quwi garini mitte mittenta maaro uyinoonni takisete asalenna qallote bikkanna maaro uyinoonni korkaata borreesse amadatenni lewu lewu aganinni qoqqowu qara odiitera ripoorte shiqisha noosi.

Gafa Honse

Takisete Ledo Xaadinohunni Kalaqamannoha Sumuu Yaate Hoonge

52. Korkaatubbate Xawishsha

Takisete seeri garinni biilloonyeho shiqinoha ayee ku'laato biilloonyu adhikki gatanno yanna adha hoogasi xawisannohu egensiishsha ku'laattosi adhinokki korkaatubba xawishsha hanqafinoha ikka noosi.

53. Takisetenna Kado Shiqqanno Gumulo Goofimarchunnita Ikkansare

1. Konni gafira worroonni amuraati garinni ikka hoogi geesha;-
   a) Takisete woy kado shiqara dandiitanno gumulo qaranna goofimarchunnita ikkitinohura ayee garinni komishiinete woy yoote mini woy wolu daanyinnatu amanyootinni giwo shiqqara dindandiitanno.
   b) Takisete shallago egensiishshi woy gumullo woy biilloonyunni takisete shallago egensiishshi gede woy gumulote hinkiilo buunxoonni sanade shiqisha takisete shallago egensiishshi woy gumulo garunni uyinoonnita ikkasi daafira hattonni takisete shallago egensiishshi woy

ወይም አሳሳች መረጃ ላይ በመመስረት ከሆነ በምህረት ቀሪ የተደረገው የታክስ ዕዳ ምህረት ከመሰጠቱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ በመመለስ ታክስ ከፋዩ ከታክስ ዕዳው ነጻ እንዳልተደረገ ተቆጥሮ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. የቢሮ ኃላፊው በዚህ አንቀጽ መሠረት እያንዳንዱን ምህረት የተሰጠበትን የታክስ ዕዳ እና የወለድ መጠን እና ምህረት የተሰጠበትን ምክንያት መዝግቦ በመያዝ በየስድስት ወሩ ለክልሉ ዋናው ኦዲተር ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

ክፍል ዘጠኝ

ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

52. የምክንያቶች መግለጫ

